በሐዘናችን ፡ ወቅት ፡ ከጐናችን ፡ ሳይለዩ ፡ ያስተዛዘኑንን ፡ ኹሉ ፥ ከቅርብም ፡ ከሩቅም ፡ የደረሱንን ፡ እና ፡ በመልእክት ፡ ያጽናኑንን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ፡ እያልን ፥ ልባዊ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርብላቸዋለን ።

እክሮይድን ፡ ሊቋቋም ፡ ለታቀደው ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማኅበረ ፡ ምእመናን ፥ በልጃችን ፡ እና ፡ በእኅታችን ፡ በወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ስም ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታችንን ፡ እናበረክታለን ። የወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ወዳጆችም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ማቋቋሚያ ፡ የሚውል ፡ ድጋፋቸውን ፡ ለማኅበሩ ፡ እንዲቸሩ ፡ በትሕትና ፡ እንለምናለን ።

እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ።

የወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ቤተሰብ ።

Account Name: St George Croydon Community
Account Number: 54333536
Sort Code: 23-05-80
IBAN: GB15MYMB23058054333536
SWIFT: MYMBGB2L



# ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ።

( 1950 ፡ ዓ.ም. ፡ - ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. )

## Mrs Mannallebiche Negga

( 1958 — 2024 A.D. )

# ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ።

## ዐጪር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ።

ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ከአባታቸው ፡ ከሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ እና ፡ ከእናታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በ 1950 ፡ ዓ.ም. ፡ ተወለዱ ።

ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኘው ፡ "ሊሴ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ትምህርት ፡ ቤት" ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ አጠናቅቀው ፥ የኹለተኛ ፡ ደረጃቸውን ፡ እንዳጋመሱ ፥ በ 1964 ፡ ዓ.ም. ፥ አባታቸው ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴነት ፡ ከባልተቤታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ልጆቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ መግሪብ ፡ ሲኼዱ ፥ ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፥ በመግሪብ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ሪባጥ ፡ በሚገኘው ፡ "ሊሴ ፡ ዴካርት" ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ አገባደዱ ።

በ 1967 ፡ ዓ.ም. ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ ፈርሶ ፡ በጊዜያዊው ፡ ወታደራዊ ፡ ደርግ ፡ ሲተካ ፥ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ዐዲሱን ፡ አስተዳደር ፡ በመቃወም ፥ ከመላ ፡ ቤተሰብ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ተሰደዱ ። ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋም ፡ እለንደን ፡ በሚገኘው ፡ በ"ሊሴ ፡ ሻርል ፡ ደ ፡ ጎል" ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለኹለት ፡ ዓመታት ፡ ቀጥለው ፥ ወደ ፡ "ዩኒቨርስቲ" ፡ መግቢያ ፡ "ባካሎሬያ"ቸውን ፡ በማግኘት ፡ ወደ ፡ ፍራንስ ፡ ተሻገሩ ። በ"ናንሲ ፡ ዩኒቨርስቲ" ፡ እና ፡ በ"ሶርቦን ፡ ዩኒቨርስቲ" ፡ በታሪክ ፡ የ"ቢ.ኤ." ፡ ዲግሪያቸውን ፡ አግኝተው ፡ በ 1977 ፡ ዓ.ም. ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ተመለሱ ። ከዚያም ፥ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ተቀጥረው ፡ እስከ ፡ 1984 ፡ ዓ.ም. ፡ ሲሠሩ ፡ ቈዩ ።

በ 1984 ፡ ዓ.ም. ፡ ከሚስተር ፡ ሮድኔ ፡ ዌብስተር ፡ ጋራ ፡ ትዳር ፡ መሥርተው ፡ በ"ኢስት-ሳሴክስ" ፡ መኖር ፡ ዠመሩ ። ከባለቤታቸው ፡ ጋራም ፡ Concrete Innovation and Design የተሠኘ ፡ ድርጅትን ፡ አቋቁመው ፡ ለሰባት ፡ ዓመታት ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፥ ለትምህርት ፡ ከነበራቸው ፡ ታላቅ ፡ ፍቅር ፡ የተነሣ ፥ በ 1991 ፡ ዓ.ም. ፥ ወደ ፡ "ዩኒበርስቲ" ፡ ተመልሰው ፥ ከሥራቸው ፡ ጋራ ፡ የሥነ ፡ ሕይወት ፡ (የ"ባዮሎጂ") ፡ ትምህርታቸውን ፡ በ"ኢስት-ሳሴክስ ፡ ዩኒቨርስቲ" ፡ ለሦስት ፡ ዓመታት ፡ ተከታትለው ፥ የ BSc. ፡ ዲግሪያቸውን ፡ አገኙ ።

እስከ ፡ 2004 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ መሥራታቸውን ፡ ቀጥለው ፥ በ 2004 ፡ ዓ.ም. ፥ ከድርጅቱ ፡ ተለይተው ፥ በ"ሀውዚንግ ፡ አሶሲዬሽን" ፡ ውስጥ ፡ በዘርፍ ፡ ኀላፊነት ፡ ላ 4 ፡ ዓመታት ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፥ በ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ National Health Service ፡ ውስጥ ፡ በሒሳብ ፡ ሠራተኛነት ፡ ለ 6 ፡ ዓመታት ፡ አገለገሉ ።

በዚህ ፡ ኹሉ ፡ የስደት ፡ ዘመን ፥ የሚወዷት ፡ ሀገራቸው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማገልገል ፡ ጽኑ ፡ ፍላጎት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፥ በተቻላቸው ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ቅን ፡ ተሳታፊ ፡ ነበሩ ። በግላቸው ፡ ደግሞ ፥ በውጭ ፡ ሀገር ፡ ተወልደው ፡ የሚያድጉ ፡ ሕፃናት ፡ ዐማርኛ ፡ መናገር ፡ እና ፡ ባማርኛ ፡ መጻፍ ፡ የሚማሩባቸውን ፡ ዘዴዎች ፡ እየፈጠሩ ፡ አበርክተዋል ። በተለይ ፡ በ 1990 ዎቹ ፡ ያሳተሙት ፡ የፊደል ፡ እና ፡ የንባብ ፡ መማሪያ ፡ ሥዕላዊ ፡ መጸሐፍ ፥ እንዲሁም ፡ "ግጥምጥሞሽ" ፡ ብለው ፡ የሰመዩት ፡ ሕፃናትን ፡ እያጫወተ ፡ ፊደልን ፡ የሚያስተምር ፡ Puzzle ፡ ጕልሕ ፡ ማስረጃዎች ፡ ናቸው ።

መጨረሻውን ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ላይ ፥ ዕድሜያቸው ፡ ለጡረታ ፡ መቃረቡን ፡ ተገንዝበው ፥ ቀሪውን ፡ ሕይወታቸውን ፡ በውድ ፡ ሀገራቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ለመጨረስ ፡ ዐቅደው ፥ ከለንደን ፡ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እየተመላለሱ ፥ ሽግግራቸውን ፡ በሚያጠናቅቁበት ፡ ወቅት ፥ ድንገተኛ ፡ ሕመም ፡ አግኝቷቸው ፥ ለሦስት ፡ ቀናት ፡ በለንደን ፡ "ሴንት ፡ ጆርጅ" ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ሲታከሙ ፡ ቈይተው ፥ ሐምሌ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ፥ በተወለዱ ፡ በ 66 ኛ ፡ ዓመታቸው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በዕረፍት ፡ ተለይተዋል ።

ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፥ ፈገግታ ፡ የማይለያቸው ፡ ፍልቅልቅ ፥ እጅግ ፡ ደግ ፣ ርኅርኅት ፡ እና ፡ ቸር ፡ ልጃችን ፡ እና ፡ እኅታችን ፡ ነበሩ ። ሰውን ፡ ማስደሰት ፡ የሚወዱ ፥ የተቸገረን ፡ ለመርዳት ፡ ዘወትር ፡ የሚጨነቁ ፥ ፍቅራቸውን ፡ በተግባር ፡ የሚያሳዩ ፥ ፍጹም ፡ ታማኝ ፡ እና ፡ ቁም ፡ ነገራም ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ነበሩ ።

የዛሬ ፡ ሦስት ፡ ሳምንት ፥ ድንገት ፡ በመጣ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መለየታቸው ፡ ለቤተሰቦቻቸው ፡ እና ፡ ለወዳጆቻቸው ፥ ለሚያውቋቸውም ፡ ኹሉ ፥ እጅግ ፡ አስደንጋጭ ፡ እና ፡ አሳዛኝ ፡ ድርስ ፡ ኾኗል ።

ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገነተ ፡ ማርያምን ፡ ነፍስ ፡ በዐጸደ ፡ ገነት ፡ ከደጋጎች ፡ ጐን ፡ ያኑርልን ።

የወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ቤተሰብ ።